# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

**ተዛማጅ መረጃዎች፡-** IEA, IEF, ISB-RA, JEA, JEA-RB, JEA-RC, JEB, JEB-RB, KLA-RA
**የሚመለከተው ጽ/ቤት፡** የት/ቤት ድጋፍእናመሻሻል፣ ዋና የአካደሚክ ኦፊሰር ጽ/ቤት

## የተማሪዎች ምደባ፣ ወደ ቀጣይ ክፍል መዛወር፣ የተፋጠነ ትምህርት ምደባ እና ባሉበት ደረጃ እንዲደግሙ ማድረግ

I. **ዓላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ክሱልስ (MCPS) ተማሪዎችን የክፍል እና የኮርስ ምደባ፣ ወደ ቀጣዩ ክፍል መዛወር፣ የተፋጠነ ትምህርት ምደባ እና ባሉበት ደረጃ የመቆየት ሂደቶችን ለማስቀመጥ

II. **ትርጉም**

U.S. የትምህርት ዲፓርትመንት በተሰጠው ትርጉም መሰረት፣ አዲስ ገቢ ማለት ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያልተወለደ እና በቅርቡ (በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ) ከቤተሰብ ጋር ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የመጣ(ች) ተማሪ ማለት ነው።

II. **ምደባ**

A. መስፈርት

1. በዚህ ደንብ ውስጥ በተቀመጠው መሰረት የዓለም አቀፍ ተማሪዎች መቀበያ እና መመዝገቢያ (IAE) ጽ/ቤት በኩል ከተመዘገቡ የተወሰኑ አዲስ ገቢ ተማሪዎች በስተቀር፣ MCPS የክፍል እና የኮርስ ደረጃ ምደባ የመጨረሻ ሃላፊነት ያለበት ርዕሰ መምህሩ ነው።

2. የተማሪን የክፍል ወይም የኮርስ ምደባ ለመወሰን፣ ርዕሰ መምህሩ ምክረ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ አግባብነት ያላቸውን ሰራተኞችን ያማክራል/ታማክራለች።

3. MCPS የተመዘገቡ ወይም ወደ MCPS የተዘዋወሩ እና የቀድሞ የትምህርት ቤት ሪከርዶችን ያላቀረቡ ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ከተማሪዎቹ እና/ወይም ከወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) ጋር ምክክር ከተደረገ በኋላ በጊዜያዊነት ይመደባሉ። ስለ ተማሪው/ዋ በቂ የሆነ መረጃ ሲቀርብ የመጨረሻ ምደባ በርዕሰ መምህሩ/ሯ ይደረጋል።

4. ከቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (Pre-K) እስከ 1ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ምደባ የሚወሰነው በስቴት ሕጎች፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች፣ እና MCPS ደንቦች መሠረት ነው። እንዲሁምየሚከተሉትን ይመልከቱ፡

    a) የቦርድ ፖሊሲJEA, ነዋሪነት፣ የትምህርት ክፍያ፣ እና ምዝገባ/Residency, Tuition, and Enrollment

b) የቦርድ ፖሊሲ IEA, የቀደምት ልጅነት እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማዕቀፍ እና መዋቅር/Framework and Structure of Early Childhood and Elementary Education።

c) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)ደንብ JEB-RB ወደ ቅድመ መዋእለ ህፃናት፣ መዋእለ ህጻናት፣ እና አንደኛ ክፍል ቀደም ብሎ ስለመግባት።

d) MCPS ደንብ JEA-RB የተማሪዎች ምዝገባ።

5. ከዚህ በፊት በሠነድ ማስረጃ የተመዘገቡ የልዩ ትምህርት ፍላጎቶች ያላቸው ተማሪዎች በሚከተሉት መስፈርቶች መሰረት ይመደባሉ፦

a) በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ላይ በተገለጸው መሰረት የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ለማግኘት የሚሠሩ ተማሪዎች እኩል ከሌለባቸው እኩዮቻቸው ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ በተገቢው ክፍል ወይም ኮርስ መመደብ

b) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ሰርተፍኬት ለማግኘት የሚሰሩ ተማሪዎች፣ በእነሱ IEP ላይ እንደተገለጸው፣ ከተማሪው(ዋ) ፍላጎቶች ጋር በተገቢው ሁኔታ በሚስማማው ክፍል ወይም ኮርስ ላይ መመደብ አለባቸው። ርዕሰ መምህራን/ተወካዮች ዲፕሎማ ለማግኘት ለማይሰሩ ተማሪዎች ተገቢ የሚሆነውን ክፍል/ኮርስ ለመወሰን እንዲረዳቸው ከልዩ ትምህርት ሱፐርቫይዘር ጋር መማከር አለባቸው።

B. IAE ምደባ

1. IAE የተማሪን የክፍል እና የኮርስ ምደባ ውሳኔዎችን መሰረት የሚያደርገው JEA-RC፣ የዓለም አቀፍ እና የውጭ ተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ ላይ በተቀመጡ መስፈርቶች ላይ ነው።

a) IAE በሌላ መልኩ እንዲወስን አሳማኝ ምክንያቶች ከሌሉ በስተቀር፣ ቀደም ሲል የነበሩ የትምህርት ክፍተቶች ወይም የእንግሊዘኛ ችሎታ ምንም ይሁን ምን፣ የአዲስ ገቢ ተማሪዎች ምደባ በተማሪ ዕድሜ ላይ የተመሰረተ ነው።

b) IAE ውሳኔ Synergy የተማሪ የማህበረሰብ ስብጥር የሚለው ምልክት (tab) ላይ ይገኛል።

2. IAE ከልዩ ትምህርት ጽ/ቤት ጋር በመመካከር፣ ከዚህ በፊት በትምህርት ማስረጃ ሰነድ የተመዘገቡ የልዩ ትምህርት ፍላጎቶች ያሏቸው IAE በኩል የተመዘገቡ ተማሪዎችን፣ ወይም የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ሊያስፈልጋቸው የሚችል እክል አለባቸው ተብለው የተጠረጠሩ ተማሪዎችን የሚመለከቱ የምደባ ውሳኔዎችን ርዕሰ መምህሩ/ሯ እንዲወስን/እንድትወስን ያስተላልፋል።

## IV. ወደ ቀጣይ ክፍል መዛወር

A. መስፈርት

1. ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ 2ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ወደ ቀጣዩ ክፍል የሚዛወሩት እድሜን መሰረት በማድረግ ነው።

2. ከ 3ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች፣ ወደ ቀጣዩ ክፍል መዛወር በአካዴሚያዊ እድገት/መሻሻል

ላይ እና ለተማሪዎች የተቀመጡ MCPS የክፍል ደረጃ ዓላማዎችን/ግቦችን ማሳካት ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

3. የሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ለማግኘ እየሰሩ ላሉት ከ 9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች፣ በሚከተሉት መስፈርቶች መሰረት፡-

   a) ወደ 10ኛ ክፍል ለመዛወር አንድ ተማሪ ለሚፈለገው የእንግሊዝኛ ኮርስ 1 ክሬዲት እና ለሚፈለገው የሂሳብ ኮርስ 1 ክሬዲት ጨምሮ ቢያንስ 5 ክሬዲቶች ማግኘት አለበት/ባት።

   b) ወደ 11ኛ ክፍል ለመዛወር፣ አንድ ተማሪ፣ በሚፈለጉት የእንግሊዘኛ ኮርሶች 2 ክሬዲቶችን፣ በሚፈለጉት የሂሳብ ኮርሶች 2 ክሬዲቶችን፣ በሚፈለገው የማህበራዊ ጥናት ኮርስ 1 ክሬዲት፣ እና በሚፈለገው የሳይንስ ኮርስ 1 ክሬዲት ጨምሮ ቢያንስ 10 ክሬዲቶች ማግኘት አለበት/ባት።

   c) ወደ 12ኛ ክፍል ለመዛወር፣ አንድ ተማሪ በሚፈለጉት የእንግሊዘኛ ኮርሶች 3 ክሬዲቶችን፣ በሚፈለጉት የሂሳብ ኮርሶች 3 ክሬዲቶችን፣ በሚፈለጉት የማህበራዊ ጥናት ኮርሶች 2 ክሬዲቶችን፣ እና በሚፈለጉት የሳይንስ ኮርሶች 2 ክሬዲቶችን ጨምሮ ቢያንስ 15 ክሬዲቶች ማግኘት አለበት/ባት።

   d) ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የምረቃ መስፈርቶችን የሚያሟሉ የሚፈለጉ ኮርሶች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የኮርስ ማስታወቂያ መፅሔት/High School Course Bulletin ውስጥ ተዘርዝረዋል።

4. ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚያገኙ እና የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ለማግኘት የሚሠሩ IEP ያላቸው ተማሪዎች ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች በመጠቀም ሁሉም ሌሎች ተማሪዎች ወደ ቀጣዩ ክፍል በሚዛወሩበት ተመሳሳይ ሁኔታ ይዛወራሉ።

B. ስልጣን/ኃላፊነት

የሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ለማግኘት እየሰሩ ያሉ IEP ያላቸው ተማሪዎችን ወደ ቀጣዩ ክፍል ማዛወር የሚወሰነው በርዕሰ መምህሩ/ሯ ነው፣ ርዕሰ መምህሩ/ሯ ይህንን ውሳኔ የሚወስነው/የምትወስነው ከተማሪዎች IEP ቡድኖች ጋር በመመካከር ይሆናል።

## V. የተፋጠነ ትምህርት ምደባ

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ወይም በክፍል ደረጃ የተማሪ ፍላጎቶች የሚሟሉት በየጊዜው የሚቀያየር ቡድን፣ ለውጥ/ማስተካከያ የተደረገበት ትምህርት እና ተጨማሪ የመማር እድሎች በመሳሰሉት የፕሮግራም ማስተካከያዎች አማካኝነት ነው።

## VI. ጣልቃገብነት/የማስተካከያ እርምጃ

A. ከቅድመ-መዋዕለ ህጻናት እስከ 8ኛ ክፍል ያለ(ች) ተማሪ MCPS የክፍል ደረጃ ወይም የኮርስ ይዘት መመዘኛዎችን/ደረጃዎችን ሳያሳካ ሲቀር ሰራተኞቹ የጣልቃ ገብነት/የማስተካከያ እርምጃ ስልቶችን ያስጀምራሉ።

1. ተማሪው/ዋ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚተገበሩት ስልቶች ምላሽ ካልሰጠ/ች፣ የትምህርት አስተዳደር ቡድን (EMT) MCPS ቅጽ 272-4፣ የትምህርት አመራር ቡድን ማጠቃለያ

አስተያየትን በመጠቀም የትምህርት ድጋፍ እቅድ ያወጣል እና ተመዝግቦ ይያዛል።

2. ወላጆች/አሳዳጊዎች እና፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ ተማሪዎች ዕቅዱን በማዘጋጀት ውስጥ ይካተታሉ።

3. ርዕሰ መምህሩ/ሯ የዚህን እቅድ አፈፃፀም ይከታተላል/ትከታተላለች።

B. ከ 9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያለ(ች) ተማሪ የኮርሱን የይዘት መመዘኛዎች/ደረጃዎች ሳያሳካ ሲቀር፣ ሰራተኞቹ የጣልቃ ገብነት/የማስተካከያ እርምጃ ስልቶችን ያዘጋጃሉ።

1. ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተማሪዎች በሂደቱ ውስጥ ይካተታሉ።

2. ርእሰ መምህሩ/ሯ ወይም ተወካይ የእቅዱን አፈጻጸም ይከታተላሉ።

3. እነዚህ ስልቶች ስኬታማ/ውጤታማ ካልሆኑ፣ የተሻሻለ የተማሪ አፈጻጸምን ለመደገፍ EMT ዕቅዱ ላይ ማስተካከያዎችን/ለውጦችን ያደርጋል።

C. በማንኛውም ጊዜ እና/ወይም በማንኛውም ክፍል አንድ ተማሪ የክፍል ደረጃ ይዘት መመዘኛዎች/ደረጃዎች እውቀትን ለማሳየት በቂ የሆነ የአካዳሚክ እድገት/መሻሻል እያሳየ(ች) ካልሆነ፣እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ የሆነ/ች ተማሪ እክል እንዳለበት/ባት ከተጠረጠረ/ች ተማሪውን/ዋን ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁ መሆኑን/ኗን ለመወሰን ተማሪውን የመገምገም አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ ለማስገባት ወደ IEP ቡድኑ ማስተላለፍ ያስፈልጋል።

## VII. ባሉበት ደረጃ ማቆየት/እንዲደግሙ ማድረግ

A. መስፈርት

1. ከቅድመ-መዋዕለ ህጻናት እስከ 2ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች፣ በሚገኙበት ደረጃ እንዲቆዩ አይደረግም። MCPS የክፍል ደረጃ ይዘት መመዘኛዎች መሰረት የማይሰሩ/የማያሟሉ ተማሪዎች ተጨማሪ እርዳታ እና ጣልቃ ገብነት/ማስተካከያ ይሰጣቸዋል።

2. ከ 3ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች፣በሚገኙበት ደረጃ መቆየት ሊታሰብ/ግምት ውስጥ ሊገባ የሚችለው እንደአስፈላጊነቱ IEP ግቦች ላይ መሻሻልን ጨምሮ EMT እቅድ እና በሰነድ የተመዘገቡ አማራጭ ትምህርታዊ ስልቶች ተማሪው/ዋ ወደ MCPS የክፍል ደረጃ ይዘት መመዘኛዎች/ደረጃዎች ለመድረስ እድገት/መሻሻል ካላሳዩ ብቻ ነው።

3. ከ 9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ከላይ IV.A.3 የተዘረዘሩትን የክሬዲት መስፈርቶች ማሟላት ካልቻሉ፣ በሚገኙበት ደረጃ እንዲቆዩ/እንዲደግሙ ይደረጋሉ።

4. IEP ለሌላቸው ተማሪዎች በሚገኙበት ደረጃ እንዲቆዩ/እንዲደግሙ ማድረግ ሲታሰብ፣ EMT፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች እና ከተማሪው(ዋ) ጋር በመሆን፣ MCPS ቅጽ 272-42፣ በሚገኙበት ደረጃ እንዲቆዩ/እንዲደግሙ ለሚደረጉ ተማሪዎች የትምህርት አስተዳደር ቡድን የፕሮግራም እቅድን በመጠቀም በሚገኙበት ደረጃ መቆየቱ/መድገሙ ለሚከሰትበት የትምህርት ዓመት አዲስ የትምህርት ድጋፍ እቅድ ያወጣል። ቀደም ሲል የተተገበረው እቅድ ውጤት በሚገኙበት ደረጃ እንዲቆዩ/እንዲደግሙ ለሚደረጉበት ዓመት ፕሮግራሙን ለማዘጋጀት መሰረት ሆነው ማገልገል አለባቸው። እንደነዚህ ያሉ ዕቅዶች ማስጠናትን፣ ማሰልጠንን/መምከርን፣ እና ሌሎች የተወሰኑ EMT ድጋፎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

5. IEP ላላቸው ተማሪዎች በሚገኙበት ደረጃ እንዲቆዩ/እንዲደግሙ ማድረግ ሲታሰብ፣ IEP ለሌላቸው ተማሪዎች ከላይ ከተገለጹት ታሳቢ መደረግ ካለባቸው ነገሮች በተጨማሪ IEP ግብ ላይ የታየ እድገት/መሻሻል እና IEP ግቦች የተካነ/ች መሆን ግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል፣ ነገር ግን፣IEP ግቦች ላይ የታየ የእድገት/የመሻሻል መጠን ወይም በግቦች የተካነ የመሆን ደረጃ አንድ IEP ያለው ተማሪ በሚገኝበት/በምትገኝበት ደረጃ እንዲቆይ(እንድትቆይ)/እንዲደግም(እንድትደግም) በሚሰጥ ውሳኔ ላይ የውሳኔው ዋና ምክንያት መሆን የለበትም።

B. ስልጣን/ኃላፊነት

1. በሚገኙበት ደረጃ እንዲቆዩ/እንዲደግሙ የማድረግ ውሳኔዎች የመጨረሻው ሀላፊነት የሚያርፈው በርዕሰ-መምህሩ/ሯ ላይ ነው።

2. ርዕሰ መምህሩ/ሯ በሚገኙበት ደረጃ እንዲቆዩ/እንዲደግሙ ማድረግን በተመለከተ የሚሰጠው/የምትሰጠው ውሳኔ የሚወሰነው፣ እንደአግባብነቱ፣ ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች፣ ከተማሪዎች፣ EMT እና IEP ቡድን ጋር በመመካከር ነው።

3. ርዕሰ መምህራን ለእያንዳንዱ በሚገኝበት/በምትገኝበት ደረጃ እንዲቆይ(እንድትቆይ)/እንዲደግም (እንድትደግም) ለተደረገ/ች ተማሪ የታቀደውን የድጋፍ እቅድ ለትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ቢሮ/School Support and Well-being ያቀርባሉ።

4. የማጠናቀቂያ ሰርተፍኬት ለማግኘት የሚሰራ/የምትሰራ ተማሪ 21 ዓመት በሚሞላቸው ዓመት በሙሉ ትምህርት መከታተል ይችላሉ እና በሚገኝበት/በምትገኝበት ደረጃ እንዲቆይ(እንድትቆይ)/እንዲደግም(እንድትደግም) ከሚያደርጉ ውሳኔዎች ነጻ ናቸው።

## VIII. ይግባኝ

A. ምደባን፣ ወደ ቀጣዩ ክፍል መዛወርን፣ ወይም በሚገኙበት ደረጃ ማቆየትን/እንዲደግሙ ማድረግን በተመለከተ ለሚነሱ ስጋቶች ወይም አለመግባባቶች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች በMCPS Regulation KLA-RA፣ ስጋቶች፣ቅሬታዎች፣ እና ይግባኞች ለትምህርት ቤቱ የበላይ ተቆጣጣሪ በኩል ቅሬታ ከማቅረባቸው በፊት ከርዕሰ መምህር እና ለተማሪው ትምህርት ሀላፊነት ካለው/ካላት ከትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ቢሮ ዳይሬክተር ጋር መፍትሄመፈለግ አለባቸው።

B. IEP ያላቸው ተማሪዎች ወደ ቀጣዩ ክፍል መዛወርን፣ ወይም በሚገኙበት ደረጃ ማቆየትን/እንዲደግሙ ማድረግን በተመለከተ የሚነሱ ስጋቶች ወይም አለመግባባቶች እክል ከሌለባቸው ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ በሆነ የይግባኝ ሂደት ውስጥ ያልፋሉ።

C. የልዩ ትምህርት እና የተዛማጅ አገልግሎቶች ምደባን ወይም አቅርቦትን በተመለከተ የሚነሱ ስጋቶች ወይም አለመግባባቶች እክል ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ህግ/Individuals with Disabilities Education Act እና በዚያ ውስጥ በተቀመጡ በደህንነት ጥበቃዎች የሚገዙ ይሆናል። ለበለጠ መረጃ ወላጅ/አሳዳጊዎች ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ከ IEP ቡድኑ፣ ከርዕሰ መምህሩ/ሯ ወይም ከአማካሪ ጋር መማከር ይችላሉ።

***ተዛማጅ ምንጮች*:** የሜሪላንድ ህጎች/ደንቦች ኮድ 13A.01.06.05, 13A.02.06.02, እና 13A.05.09.03።

**ደንቡ የተሻሻለባቸው ጊዜያት፡-** የቀድሞው ደንብ 3553፣ ሜይ 15, 1981፣ የማውጫ መረጃ ተሻሽሏል፣ ዲሴምበር 1986 ተሻሽሎ ወደ ሁለት ደንቦች ተከፍሏል (ይሄኛው እና JEA-RB) ኦገስት 26, 1987፤ ኤፕሪል 1, 1992 ተሻሽሏል፣ የተሻሻለው ማርች 23, 2010፣ ኦገስት 22, 2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድእንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-
U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024